<u>በአንድነት እናመስግነው</u>

በአንድነት እናመስግነው መድኃኒዓለምን (፪)
እንዳንተ ያለ ፍፁም ማንም የለም እያልን (፪)

እንዳንተ ያለ ፍፁም መግደልና ማዳን የሚቻለውን
» » » ህይወትና ሞትን በእጁ የያዘውን
» » » መንፈሳዊ ፀጋ የሚሰጠውን
እንደሰው ያልሆነ አድልዎ የሌለበትን

አዝ...

እንዳንተ ያለ ፍፁም የአዳም ልጆችን መጥቶ ያዳነውን
» » » ከድንግል ማርያም ሰው የሆነውን
» » » ትንሣኤና ህይወት የሆነውን ጌታ
ከሰይጣን አላቆ ሆኖናል መከታ

አዝ...

እንዳንተ ያለ ፍፁም ለፍጥረቱ ህይወትን ሞቶ ያደለውን
» » » የህይወት እንጀራ ሆኖ የመጣውን
» » » ለንስሃ ኃጥአንን ሊጠራ ለመጣው
ለፍጥረቱ ኃይልን ስርየትን ለሰጠው

አዝ...

እንዳንተ ያለ ፍፁም ለንስሃ እድሜን የጨመረልንን
» » » እንደ ኃጥያታችን ፈርዶ ያላጠፋንን
» » » ለልዑል እግዚአብሔር ለኃያሉ ንጉሥ
እልል እልል እንበል ስሙን እናወድስ

አዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org